# የበረከት ወጎች

*አሜን ተፈሪ*

*እና ምርጫ 97፣ ኢህአዴግ ከናዳው ፍጥነት በላይ በመሮጥ ደማቅ ብርሃን መፍጠር ያልቻለበት፣ ጨርሶም እንደ ዔሊ በማዝገም በናዳው ያልተጨፈለቀበት፣ ብርሃን እና ጨለማ ጎን ለጎን የቆሙበት ሁኔታ ውስጥ ገባ።*

## መግቢያ

«የሁለት ምርጫዎች ወግ»ን በማስተንተን ዓይን ተመልክቶ ለመረዳት የሚሞክር ሰው፣ አንድ ስውር የታሪክ ቅኔ ይመለከታል። በትረካው የተነሳው ታሪክ ዞሮ የሚገጥም ትልም አለው። አቶ በረከት በ«የሁለት ከተሞች ወግ» የገለፁት ታሪክ የሚነሳው፣ ከኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ነው። ይህ ጦርነት በኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ዘንድ የትንታኔና የአመለካከት ልዩነት እንደ ፈጠረ፣ ልዩነቱም የሃሳብ ትግልን እንደ ቀሰቀሰ፣ የሀሳብ ትግሉም ባላንጣ የሚያደርግ የአቋም ልዩነትን እንደ ወለደ፣ ይህም ወደ መከፋፈል እንዳመራ ይተርኩልናል።

ከትረካቸው የምንረዳው፣ በሁለት ወገን የቆመው የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ያካሄደው የተጋጋለ የሃሳብ ፍልሚያ፣ ዘመን የሰጠውን ግዳጅ ፈፅሞ ማንጎላጀት የጀመረውን አብዮት በድንገተኛ የ«ብራ መብረቅ» ከእንቅልፍ ቀስቅሶት፣ የማያቋርጥ ራስን የማየት ሂደት ውስጥ እንዲገባ ገፋፍቶት፣ ያልሰራውን ብቻ ሳይሆን «ሰራሁ ጨረስኩ» ያለውን ሁሉ ዳግም ለመፈተሽ እንዲነሳ እንዳደረገው ነው።

በዚህም ወደ ኋላ የመመለስ አደጋን ተሻግሮ ወደ ፊት ለመሄድ የሚያስችልና ለህዳሴው ንቅናቄ መሰረት የሆነ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ርዕዮት መፍጠሩን፣ ከህዳሴው ባቡር ተንሸራተው የወደቁትንም «ሙታንን ተዋቸው፣ ሙታናቸውን ይቅበሩ» ብሎ ጉዞ መቀጠሉን እንረዳለን።

«የሁለት ከተሞች ወግ» የምርጫውን ሂደትና ውጤት የወሰኑ ጉዳዮችን ከመተንተን ይነሳል። የኤርትራ ጦርነት፣ በድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ዘንድ የአቋም ልዩነት እንዲፈጠር ያደረገ ነበር። በዚህም ረጅም የሀሳብ ትግል ተፈጠረ። ከዚህ ትግል «የተሀድሶ ልጆች» ተወለዱ። የሃሳብ ትግሉም «በበህዳሴው ልጆች» አሸናፊነት ተደመደመ።

«የተሀድሶ ልጆች» በልማት እጦት እና በመልካም አስተዳደር ችግሮች የተነሳ ለተስፋ መቁረጥ የተዳረገውን ህብረተሰብ ተስፋ ማለምለም ወይም ኢህአዴግ «የአርማጌዶን ክስተት» ሲል የሚጠቅሰውን አደጋ ማስወገድ ነበረባቸው። ይህም ችግር በጎዳና ላይ ነውጥ እየታየ ነበር።

ይህን ሁኔታ በውል በመገንዘብ «የኢህአዴግ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ በከተማ የሚንተከተከው የአመጽ ስሜትና ገጠሩን ሰፋ አድርጎ ካካለለው ድርቅ ጋር ተያይዞ የመጣው ፈታኝ ሁኔታ በፍጥነት ካልተቀየረ በስተቀር እንደ አገር መጥፋታችን ነው፣ የሚል ስምምነት ላይ ደረሰ» (37)። ይህን አደጋ ለማስወገድና ችግሩን ለመከላት መፍትሄ ይሆናል ብሎ የነደፈውን ፖሊሲና ስትራቴጂ በከፍተኛ ፍጥነት ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ ጀመረ። ሆኖም የተሀድሶው እንቅስቃሴ የፈጠረው የብርሃን ጭላንጭል ገና ደምቆ መታየት ባልጀመረበት ጊዜ ምርጫ ዘጠና ሰባት ከተፍ አለ።

# የሃሳብ ፍልሚያ

ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ በኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ውስጥ የተነሳው የሃሳብ ፍልሚያ ሁለት ተቃራኒ ትንተናዎች የተራመደበት የሁለት ጎራዎች ፍልሚያ ነበር። አንደኛው ወገን፣ የስርዓቱ አደጋ ውስጣዊ፣ አገራዊ እና ድርጅታዊ ችግር ነው (29) የሚል አቋም ይዟል። ሌላኛው፣ «የለም ዋናው የስርዓቱ አደጋ ምንጭ ውጫዊ ነው» ይላል። ስለዚህ፣ በሁለቱም ወገኖች የተለያዩ ፅሁፎች ተፅፈው እየቀረቡ ክርክር ተካሄደ። የእነ አቶ ስዬ ወገን፣ «ተንበርካኪ እና ከሃዲ» ሲል የእነ አቶ መለስን ወገን ይከሳል። የእነ አቶ መለስ ወገን ደግሞ፣ «ውህዳን፣ አንጃ እና ጀብደኛ» በማለት ይፈርጃል።

የእነ አቶ ስዬ ወገን ድርጅታዊ መሠረት በየጊዜው እየተሸረሸረ መጥቶ፣ በመጨረሻ አንጃው «...የውይይት መድረኮችን ረግጦ በመውጣት ራሱን ከድርጅቱ አገለለ» የሚሉት ደራሲው፣ በማስከተል፣ «የተከፈተው ይህ የክርክር መድረክ፣ የአመራር አባላትን ለአስር ዓመታት ካንጎላጁበት ድባብ አውጥቶ ለምሁራዊ ምርምር እና ጥልቅ ዕውቀት በማጋለጥ በኢህአዴግ ውስጥ በጣም ልዩ የሚባል ርዕዮተ ዓለማዊና ፖለቲካዊ ህዳሴ አጋጣሚ ፈጥሯል።» ሆኖም፣ «...ከመድረኩ ረግጦ የወጣው ኃይል በዕድሉ ሳይጠቀምበት ቀረ» ይሉናል።

«በአንፃሩ፣ በድርጅቱ ውስጥ ቆይቶ በክርክሮቹ ውስጥ ያለፈው ኃይል እንደ ሰይፍ ተስሎ ከመውጣቱም በላይ በስርዓቱ አደጋዎች እና መፍትሄዎች ላይም መግባባት ላይ ደረሰ» (29) ብለዋል።

ታዲያ በሃሳብ ትግሉ አሸናፊ ሆነው የወጡት «የህዳሴው ልጆች»፣ «የአገሪቱ ችግሮች ዋነኛ ምንጮች...» የሚሏቸው ነገሮች አሉ፡፡ ደራሲው ስለዚህ ጉዳይ ሲተርክ፣ «...በህብረተሰባችን አወቃቀር እና በምንገኝበት የዕድገት ደረጃ ምክንያት በስርዓቱ ላይ የጥገኛ ዝቅጠት አደጋ አንዣቦብናል...» (25) ይላሉ፡፡ እናም «የህዳሴው ልጆች» ይህ ሁኔታ በስርዓቱ ላይ የጋረጠው ትልቅ አደጋ እየታያቸው ይሰጋሉ፡፡

የሥጋት ትንተናውም ከ1848 የፈረንሳይ አብዮት ጋር ተነፃፅሮ የቀረበ ነው፡፡ በሉዊ ቦናፓርት ዘመን እንደ ነበረው በጀማሪ ደረጃ ላይ የሚገኘው የሀገራችን ካፒታሊዝም፣ የዳበረ ካፒታሊዝም ከፈጠሩ ሀገሮች ጋር በንጽጽር ሲታይ፣ ለሁሉም ሰው በቶሎ የመበልጸግን ሰፊ ጎዳና የሚከፍት ነው፡፡ ከላይ ወደ ታች፣ ከታችም ወደ ላይ የሚምዘገዘግ የማህበራዊ ሽግሽግ [Social mobility] ሂደት የሚታይበት ነው፡፡ አቶ በረከት ይህን ብለው፣

«...በዚህ አጋጣሚ ተጠቅሞ በህጋዊም ሆነ በህገ ወጥ መንገድ ለመበልጸግ መሯሯጥ የሚበዛበት... ስለዚህ በሉዊ ቦናፓርት ዘመን እንደ ታየው በመንግስት ሥልጣን ላይ ያሉ ኃይሎች ስልጣናቸውን በመጠቀም ከፍተኛ ሀብት ለማግበስበስ እና ራሳቸውን ወደ ባለ ሀብትነት ለመቀየር የሚችሉበት፣ በዚህም ራሱን አበልፅጎ ወደ ገዢ መደብነት ለመቀየር የሚተጋበት ሁኔታ ይኖራል» (26)፡፡ ስለዚህ በፈረንሳይ የሊዊ ቦናፓርት ዘመን እንደ ታየው በእኛም ሀገር ለጥገኛ ዝቅጠት በር የሚከፍት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ስለዚህ ደራሲው፣ «... ኢህአዴግና በእርሱ የሚመራው መንግስት ካልተጠነቀቁ በስተቀር የመንግስት ሥልጣን ይዞ፣ ሌላውን ህዝብ በነበረበት የኢኮኖሚ ማጥ ውስጥ አቆይቶ በአቋራጭ የመክበር ጉዳይ ከፊታቸው የተደቀነ አደጋ ሆኖ ተቀምጧል» (27) ይላሉ፡፡

እንደ ሊዊ ቦናፓርት ከፍተኛ የአርሶ አደር ድጋፍ ያለው ኢህአዴግ፣ የብሄር እኩልነት እና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን የመለሰው ኢህአዴግ፣ ከአርሶ አደሩ ድጋፍ እንጂ ተቃውሞ የማይገጥመው ኢህአዴግ፣ ቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት ውስጥ ሊዘፈቅ የሚችልበት ምቹ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አለ፡፡ እንዲህ ባለ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ የመንግስት ስልጣን ይዞ አገር የሚያስተዳድረው እና በአብዛኛው ከንዑስ ከበርቴ መደብ የወጣው የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር ያለው ባህርይ እና ማህበራዊ ዝንባሌ ለጥገኛ ዝቅጠት አደጋ በቀላሉ የሚያጋልጠው መሆኑንም ይጠቅሳሉ፣ (ገፅ፣28)፡፡

«የመንግስት ስልጣን ይዞ፣ በቢሊየኖች የሚቆጠር የአገር ገንዘብ የሚያንቀሳቅሰው፣ በቢሊየኖች የሚቆጠር ገንዘብ በሚፈስባቸው ጨረታዎች እና ግዢዎች ላይ ውሳኔ የሚያሳልፈው፣ በሚሊየኖች የሚቆጠር የአርሶ አደር ኃይል ላይ የማዘዝ ሰፊ ሥልጣን ያለው የኢህአዴግ

አመራር ጤናማ ሆኖ፣ የፖለቲካዊ ሥልጣንን ለልማትና ለህዝብ ተጠቃሚነት ሊያውለው ካልቆረጠ በስተቀር፣ በራስ ወዳድነት ወደ ግሉ ሊያዘነብል የሚችል ነው፡፡... ይህ አመራር ለሥጋው ያደረ አመራር ከሆነ፣ የብዙሃኑን ጉስቁልና በማባባስ እና ከዚያም አልፎ ዕድገታችንን በማደናቀፍ ጠቅላላ ሀገሪቱን ይዞ ወደ ጥፋት ሊወስዳት ይችላል» ይላሉ፡፡ (28)

በዚህም የተነሳ፣ ከ1993 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ከአመራሩ አልፎ በመላ ድርጅቱ የተከሰተው የውስጥ ትግል በ1994 ዓ.ም ለወጡት ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መነሻ ሆኗል፡፡ በዚህም መሠረት ትግሉ ለፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ የማዕዘን ድንጋይ በሆነ የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ንድፍ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ትግል መቀጠሉን ደራሲው ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ሰነዶችና የድርጅቱ አባላት በሰነዶቹ ላይ ያደረጉት ውይይት በትጥቅ ትግል ዘመን ከተያዘው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም የተንጠባጠቡ አስተሳሰቦች የተሻሩበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ድርጅቱ ካፒታሊስታዊ ስርዓት ለመገንባት ቆርጦ መነሳቱንም በይፋ አበሰረ፡፡ በዚህም መሰረት ከህዳር 1994 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ አምስት መሰረታዊ የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶች ተዘጋጁ፡፡ እነሱንም ተግባራዊ ለማድረግ ርብርብ ተጀመረ፡፡

## ከናዳ የማምለጥ ሩጫ

ሆኖም ከተሃድሶ ዘመን በፊት ባሉት አስር ወይም አስራ ሁለት ዓመታት በቂ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ባለመሰራታቸው የተነሳ በህብረተሰቡ ውስጥ በተለይም በከተማ ነዋሪው ዘንድ እየተባባሰ በመጣው ብሶት፣ ተስፋ መቁረጥና ሌሎች ተዛማጅ ችግሮች ምክንያት የተሀድሶ እንቅስቃሴው አደጋ ተጋርጦበታል፡፡ ድርጅቱ ይህን አደጋ «አርማጌዶን» በሚል ሰይሞታል፡፡

የኢህአዴግን መከፋፈል ተከትሎ በ1993 ዓ.ም ሚያዚያ ወር አዲስ አበባ በድንገተኛ ነውጥ ተመታች፡፡ ንብረት ተዘረፈ፣ የከተማ አውቶብሶችም ጋዩ፡፡ እናም ኢህአዴግ፣ «በየዓመቱ በአመፅ ቋፍ ላይ ሆኖ የሚንተከተክ ህብረተሰብ ይዘን፣ በትንሽ በትልቁ ሰበብ የጎዳና ላይ ነውጥ ሊደጋገም የሚችልበት ዕድል መኖሩም ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ አደረገው» (33) ይላሉ፣ ደራሲው፡፡

«የተሀድሶ እንቅስቃሴው በተለኮሰ ማግስት... አራት ሚሊዮን ያህል ህዝብን ለአደጋ ያጋለጠ ድርቅ ተከሰቶ ነበር» (34)፡፡ ይህን ተጨባጭ ሁኔታ የገመገመው መንግስት የዚህ ችግር ዋነኛ መፍትሄ አገራችንን በፍጥነት «ማልማት ነው» የሚሉት አቶ በረከት፣ ድርቁ የተከሰተው ከአውዳሚው የኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ማግስት በኋላ በመሆኑ መንግስትን ለውጭ ተፅዕኖና ለውስጥ ውጥረት እንዳጋለጠው ይተርካሉ፡፡ የአርሜዶን ምልክቶች ተደራርበው መምጣት

የኢህአዴግን አመራር «ጊዜ የለንም» የሚል ጥድፊያ ውስጥ አስገባው:: ብዙም ሳይቆይ ወደ ምርጫ 97 ገባ::

ይህ፤ «...የተጋጋለው የምርጫ ሂደት፣ ለህገ- መንግስቱ ታማኝ በሆኑ ፓርቲዎች እና ህገ-መንግስቱ ባኃይልም ቢሆን መቀየር አለበት ብለው በሚያምኑት ተቃዋሚዎች መካከል አልህና መገታተር የበዛበት፣ ከፍተኛ ፉክክር...» ሆነ (ገፅ፣ 82)::

በመጨረሻም፤ የምርጫ ዘጠና ሰባት ናዳ ኢህአዴግን አንገዳግዶት አለፈ:: ተቃዋሚዎች ግን ከፍተኛ እመርታ ያገኙበት ሆነ:: ሆኖም ተቃዋሚዎች፤ ከ12 ወደ 170 ወንበር ያሳደጋቸውን የድምጽ ውጤት አልተጠቀሙበትም:: በተቃራኒው ወደ አመጽ አመሩ:: ፍፁም ሰላማዊ ሆኖ እስከ ድምጽ መስጠት የደረሰው የምርጫ ሂደትም ደፈረሰ:: ኢህአዴግ የጎዳና ላይ ነውጥ እንዳይመጣ፤ ከመጣም በኋላ የህዝብ ልጆች ህይወት እንዳይጠፋ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶችን ማድረጉን የሚገልፁት አቶ በረከት ይህ ጥረት አለመሳካቱን ይተርካሉ::

ያም ሆኖ ኢህአዴግ ችግሩ ወደ ጠቅላላ ቀውስ እንዳይሄድ የውይይትና የድርድር መድረኮችን በመፍጠር ብዙ ጥረት አደረገ:: የቅሬታ ማጣሪያ ስርዓት በመዘርጋት ቅሬታዎች ተጣርተው የዳግም ምርጫ እንዲካሄድ አደረገ:: ከሃያ አንድ ወራት የግማሽ ማራቶን ሩጫ በኋላ የ97 ነገር ተቋጭቶ «ወደ ልማት ፊታችንን አዞርን» በማለት የክፍል አንድ ትረካቸውን ይዘጋሉ:: እናም ወደ ቀጣዩ የ2002 ምርጫ ይሻገራሉ::

- ## *ምርጫ 2002*

በህዳሴው ባቡር እንዳይሳፈር ሲታገሉት የነበሩት እና ከትግል መድረኩ የሸሹት ወገኖች፤ በሂደቱ ተስለው የወጡት «የህዳሴው ልጆች» በህዳሴው ጎዳና በድል ተረማምደው፤ ምርጫ ዘጠና ሰባትን ተሻግረው፤ ከምርጫ 2002 ሲደርሱ፤ በህዳሴው መባቻ በአካል የታገላቸው ኃይል መልክ ቀይሮ አና ቅርፅ ሰብሮ ዳግም በጣዕረ መንፈስ ሲታገላቸው የምናይበት ትረካ ነው::

ደራሲው አቶ በረከት ስምኦን፣ የምርጫ ዘጠና ሰባት ሂደትን ከ2002 ምርጫ ጋር እያነፃፀሩ ይተርካሉ:: በአጠቃላይ የምርጫውን ሂደት ለመተረክ፣ ለመፈከር (interpret)፣ ለመተንተን (analysis)፣ በዚህም እውነታውን ለመረዳት በብዙ ድርጊቶች የታጨቀውን የታሪክ ዘመን ይዘት ለመገንዘብ የሚበጅ መላ ያደረጉት የንፅፅር (comparison) ትንተናን ነው::

የምርጫ 2002 ትረካ፤ በምርጫ ዘጠና ሰባት ትረካ የተገለፀው ትንታኔና ድምዳሜ ትክክል መሆኑን የምናይበት ነው:: የ97 ምርጫ ውጤትን የወሰኑትና የኢህአዴግን የምርጫ ውጤት

ያበላሹት ነገሮች ሲወገዱ ሁኔታዎች ሁሉ መለወጣቸውን ያሳየናል። በተገኘው ትምህርት እንዴት የተለወጠ ውጤት ሊያመጣ እንደ ቻለ በማሳየትም እስከ ፍፃሚው ይወስደናል።

በ2002 ዓ.ም ምርጫ ኢህአዴግ ስህተቶቹን አርሞ እንደ መጣና የተቃማዊው ጎራ ግን የአስተሳሰብ ሳይሆን የመልክ ለውጥ ይዞ እንደ መጣ የሚያጫውቱን አቶ በረከት፣ «የጀብደኝነት ልጆች» አንጃ ፈጥረው ከድርጅቱ ከወጡ በኋላ፣ «መድረክ» በተሰኘው የፓርቲዎች ስብስብ ገብተውና እርሱን ወክለው ለውድድር ቢቀርቡም በዝረራ መሸነፋቸውን ያወጉናል።

በሌላ በኩል፣ ህዝብ እና ኢህአዴግ ከቀዳሚው የምርጫ ሂደት ትምህርት በመቅሰም የዘጠና ሰባትን ውጤት ሲቀይሩ እንመለከታለን። በዘጠና ሰባት ምርጫ ብሶት ሲያሰማ እና «ሥራ አበዛችሁብኝ» በማለት ሲያማርር የነበረው አርሶ አደር፣ «አመራሮቻችን ለኛ ባደረጉት መልካም ነገር ሁሉ ልንሸልማቸው ይገባ ነበር። ነገር ግን የእነሱ ሽልማት የኛ መሻሻል ነው» (ገፅ፣310) ሲሉ እንሰማለን። ኢህአዴግም «ለዘመናት በማሽቆልቆል ጉዞ ውስጥ የነበረችውን አገር ሽቅብ ዳገቱን መውጣት እንድትጀምር ማድረግ (ገጽ፣ 310) የቻለ መሪ ድርጅት መሆኑን እንመለከታለን።

# ሦስቱ ኃይለ ቃላት

አሁን የትንታኔው ማጠንጠኛ ወይም የትረካው ፈር ቀዳጅ የሆኑ ጉዳዮችን ለማየት እሞክራለሁ።

እንደኔ ንባብ፣ የትረካ ጉዞውን እና ትንታኔውን የወሰኑ ሦስት ኃይለ ቃላት አሉ። አንደኛው፣ አቶ መለስ ለሥራ አስፈፃሚ ባቀረቡት ሪፖርት የተጠቀሙበትና በመጽሀፉ የጀርባ ሽፋን ገጽ ላይ ሰፍሮ የሚነበበው ሀሳብ ነው። ሁለተኛው፣ ቻርልስ ዲከንስ በ«ሁለት ከተሞች ወግ» «ብርሃን እና ጨለማ»ን በአንድ አጣምሮ የያዘ ማህበራዊ እውነታን ለመግለፅ የተጠቀመበት ገለፃ ነው። ሦስተኛው፣ የሽግግር ዲሞክራሲ ህብረተሰብ ልዩ ገጽታ ነው።

አቶ መለስ ለድርጅታቸው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባቀረቡት ሪፖርት፣ «የተሃድሶ እንቅስቃሴያቸውን በከፍተኛ ፍጥነት ከሚወርድና በየደቂቃው ፍጥነት እየጨመረ ከሚጓዝ ናዳ አምልጦ ወደ ጠንካራ ከለላ ለመግባት ከሚሮጥ ሰው ጋር ማመሳሰል ይቻላል። ይህ ሰው ከለላው ያለበትን አቅጣጫ አውቆ ወደዚያ የሚያመራ አቋራጭ መንገድ ይዞ ካልተጓዘ ስተቀር በናዳው እንደሚደፈን ምንም ጥርጥር የለውም።... ሰውዬው ከናዳው ፍጥነት በላይ መሮጥ ካልቻለ ባለበትም ቢቀበር፣ ወደ መጠለያው ለመግባት አንድ እርምጃ ሲቀረውም ቢቀበር

ለውጥ የለውም፡፡ … [ስለዚህ] የፍጥነት ጉዳይ ከአቅጣጫ ባላነሰ መንገድ የህልውና ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ …ከአደጋው ለማምለጥ የሚያስችል ብቃት ያለው ፍጥነት ወሳኝ የሚሆንበት ሁኔታ አለ…፡፡ እኛም …ቀና መንገድ ይዘን ከአደጋው ለማምለጥ የሚያስችል ፍጥነት ስለሌለን በእርግጠኝነት የምንሸነፍበት አደጋ ነው እየተከሰተ ያለው» (ገጽ38) የሚለው የአቶ መለስ ቃል፣ አንድ የትንታኔ ማዳወሪያ ሆኖ ቀርቧል፡፡

አቶ መለስ የተሃድሶ እንቅስቃሴውን ከናዳ ለማምለጥ በሚሮጥ ሰው መስለው ያቀረቡት ትንታኔ «አመራሩ ጊዜ የለንም በሚል ጥድፊያ ውስጥ እንዲገባ አደረገው» (38) የሚሉት ደራሲው፣ «አርማጌዶን ፈጦ በወጣበትና አገሪቱን ወደ ህዳሴ ሊያመሩ የሚችሉ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በተነደፉበት [ሁኔታ] አመራሩ አገሪቱን ይዞ ከአደጋው ለማምለጥ በከፍተኛ ጥድፊያ ለመሮጥ… የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች በአንድ ላይ ተገጣጠሙ» (39) ይላሉ፡፡

እናም አመራሩ ከናዳው ለማምለጥ በ1995 ዓ.ም የክረምት ወራት አህዱ ብሎ ሩጫውን እንደ ጀመረ የሚገልፁት ደራሲው፣ «ይህ እንቅስቃሴ የሁለቱን ምርጫዎች ይዘትና ውጤት እንዴት እንደ ወሰነ ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡

ሁለተኛው የትንታኔ ምሰሶ፣ ቻርልስ ዲከንስ «እሣት እና ጭድ» የሆኑ ነገሮች ተዳብለው የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመግለፅ የተጠቀመበት ኃይለ ቃል ነው፡፡ እንዲህ እያለ፣ «ወቅቱ ከመቼውም የተሻለ ነበር፡፡ ከወቅቶች ሁሉ የከፋውም ነበር፡፡ የብስለት ዘመን እንደ ነበረው ሁሉ፣ የየዋህነትም ዘመን ነበር…» (45) የሚለው ገለፃ ሌላ የትንታኔ ማዳወሪያ ሆኖ ታይቶኛል፡፡

ሦስተኛው፣ በሽግግር ዘመን ህብረተሰብ ዘንድ የሚታየው ባህርይ ነው፡፡ ይህን እንደ አንድ የትንታኔ ፈለግ የያዙት አቶ በረከት የሽግግር ዘመን ባህርይ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ሲንፀባረቅ ያሳዩናል፡፡

በጀማሪ የካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ የሚታይ ማህበራዊ አወቃቀር የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች በሚያቀርቡት የትንተና ፅሁፍ ውስጥ የሚጠቀስና ከዚያም በኋላ፣ «…እውነተኛ የሽግግር ወቅት ገበሬ» (72)፣ «ዋናው ጉዳይ ራሱ ባለ ሀብቱም የሽግግር ወቅት ባለሀብት መሆኑ ነው» (ገጽ፣38) እንዲሁም፣ ቅንጅትንና ኢህአዴግን በመደገፍ በሚያዚያ ወር የተካሄደውን የሰላማዊ ሰልፍ አስመልክተው ሲናገሩ «…ኢህአዴግን ደግፈው የተሳተፉትም ቢሆን በዚህኛው ሰልፍ ላይ መገኘታቸውን አምነናል፡፡ ደግሞስ የሽግግር ወቅት አይደል?»

(ገጽ፣88) ይላሉ፡፡ ይህም የሽግግር ወቅት አንድ የትንታኔ ማጠንጠኛ ሀሳብ መሆኑን ያመለክተናል፡፡

# ትንታኔው

ሀገሪቱ የአርማጌዶን አደጋ እንደ ተጋረጠባት ይህን አደጋ ለማምለጥ «ከናዳው ፍጥነት በላቀ ፍጥነት መሮጥ አስፈላጊ መሆኑን፤ ይህ ካልሆነ የሀገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ችግር እንደሚከተል አምኖ በጥድፊያ መሮጥ ተጀመረ» ይላሉ አቶ በረከት፡፡

«ኢህአዴግ በአገራችን የአርማጌዶን ዓይነት ጥፋት እንዳይከሰት ለማድረግ በአጭር ታጥቆ በተነሳበት ጊዜ የጥፋት ምልክቶች ጎልተው መታየት መጀመራቸው አገሪቱ ጊዜ እንደሌላት አመላካች ነበር፡፡ በእርግጥም የተስፋ መቁረጥ፣ የጭንቀት ሁኔታን በፍጥነት ካልፈታው በስተቀር፤ ተስፋ የቆረጠና በሽንቁሩ ማዶ የብርሃን ጭላንጭል የማይታየው ህዝብ ወደ ቀውስ እንዳያመራ የሚያደርግ አስተማማኝ ዋስትና የለም» (ገጽ፣ 36) ይላሉ፡፡

ደራሲው፤ «በተሀድሶ መድረክ የፖሊሲና የስትራቴጂ ችግርን» ፈታሁ. ቢልም፤ የማስፈፀም ጉዳይ አስጨንቆታል፡፡ ከማስፈፀም አቅም በላይ የጊዜ ጉዳይ እጅግ አሳስቦታል፡፡ እናም ኢህአዴግ «ጊዜ የለንም» የሚል ጥድፊያ ውስጥ ገብቷል ይሉናል፡፡

# ጥድፊያ - በገጠር

አቶ መለስ ከናዳ ለማምለጥ በሚሮጥ ሰው ምሳሌ ያቀረቡት ትንታኔ በአመራሩ ዘንድ እንቅልፍ የሚነሳ ስሜት ፈጥሮ፤ ሩጫው በ1995 የክረምት ወር ተጀመረ፡፡ ጥድፊያው በገጠርም በከተማም ነው፡፡ በገጠሩ ሥራ የግብርና ባለሙያ የሆነውም- ያልሆነውም ገባ፡፡ ግብርናን የማያውቀው ለማወቅ፤ ቢያንስ የእነርሱን ሥራ ለመደገፍና ምቹ ፖለቲካዊ ማዕቀፍ ለመፍጠር ተሯሯጠ፡፡ በመጀመሪያ ለአርሶ አደሩ ያቀረቡለት ምክር፤ «መሬቱን ደጋግሞ እንዲያርስ፣ ሁለትና ሦስት ጊዜ እንዲያርም፣ ከወፍ እንዲጠብቅ፣ ካልተጠበቀ ዝናብ አዝመራውን እንዲከላከል» (39) ነበር፡፡

በሰማንያዎቹ የተጀመሩትን የግብርና ዘዴዎችን እንደገና ማስተማር ያዘ፡፡ በዚያ ላይ የዝናቡ ጥሩ መሆን አግዟቸው፤ «...በተደረገው ከፍተኛ ጥረት በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ

የምርት ጭማሪ አስገኘ ። በዚያ የምርት ዘመን ኢኮኖሚው የ11.7 በመቶ ዕድገት አስመዘገበ» (ዝኒ ከማሁ)።

በዚህች ጥረት ከፍተኛ ለውጥ በማግኘታቸው ተበረታቱ። በዓመት ከመቶ ሃምሳ ቀናት በላይ የማይሰራው እና በጋውን ቁጭ ብሎ የሚያሳልፈው አርሶ አደር የበጋ ሥራ እንዲጀምር ለማድረግ፣ ምቹ በሆነ አካባቢ ደግሞ የመስኖ ሥራ እንዲስፋፋ ለማድረግ ጥረት ተደረገ።

በዚህም አርሶ አደሩ የሥራ ጊዜውን በእጥፍ ጨመረ። ምርታማነቱም አብሮ በእጥፍ አደገ። እናም በቀጣዩ ዓመት የ12.6 በመቶ ዕደገት ተመዘገበ።

ታዲያ «ምርጫ ዘጠና ሰባትን የተቀበልነው በገጠር የሁለት ዓመታት ተከታታይ ከፍተኛ ዕድገት አስመዝግበን ነው» የሚሉት አቶ በረከት፣ «...በከተሞች ግን ሥራ ጀመርን ማለት የሚቻለው በ1996 ዓ.ም አጋማሽ ብቻ ነበር» ብለዋል።

# ጥድፊያ - በከተማ

በከተማም ተመሳሳይ ጥድፊያ ተጀመረ። ኢህአዴግ ከተሞችን በገጠር ስሌት ሲመራ እንደቆየ የሚገልፁት አቶ በረከት፣ ይህን አሰራሩን ለመቀየር መወሰኑን ይናገራሉ። ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልፁም፣ «...ኢህአዴግ በከተሞች የአርማጌዶን ምልክቶች እየተጠናከሩ መምጣታቸውን ከታዘበ በኋላ አመራሩን ከመቀየር ጀምሮ ከተሞችን ወደ ተፋጠነ የዕድገት ምህዋር የሚያስገባ እንቅስቃሴ ተከተለ» (ገጽ፣ 44) ይላሉ። ይህም ሥራ የተጀመረው በአዲስ አበባ በመሆኑ፣ «ከየክልሉ ከተማ ቀመስ ሰው እየተፈለገ ተመልምሎ መጥቶ አዲስ አበባ እንዲገባ ተደረገ» ብለውናል።

ከተሞችን እንደ ገጠር ሳይሆን እንደ ከተማ ለመምራት በተደረገው ጥረት አደረጃጀቱን በመቀየር፣ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ሥራዎች ተጀመሩ። በከተሞች የጋራ መኖሪያ ቤቶችን የመገንባቱ ሥራ እንደ አንድ ቁልፍ ሥራ ተወስዶ ርብርብ ተደረገ። ለወጣቶችም ሰፊ የሥራ ዕድል ተፈጠረ። በአጠቃላይ የአዲስ አበባ ትንሳዔ ተበሰረ ይላሉ። አያይዘውም በእነ አቶ አርከበ ዘመን «በአዲስ አበባ የተጀመረውን የተፋጠነ ልማት በሌሎችም ክልሎች የማላመድ ሙከራው የቀጠለ ቢሆንም፣ በዚህ ረገድ እስከ ምርጫ 97 ድረስ ትርጉም ያለው ሥራ ተሰርቷል ማለት አይቻልም» (ገጽ፣ 45) ብለዋል። እናም በገጠር የሁለት ዓመት ዕድገት፣ በከተሞች ደግሞ ገና ለውጡ እንደ ተጀመረ ምርጫ 97 መጣ።

ስለዚሁ ሁኔታ አቶ በረከት ሲገልፁ፤ «በኢትዮጵያ የህዳሴ ብርሃን መፈንጠቅ በጀመረበት፤ ሆኖም ከብርሃኑ የሚፈልቀው ሙቀት የአገሪቱን ህዝቦች ከቆፈን ማላቀቅ ባልጀመረበት ወቅት ነው፤ ምርጫ 97 የደረሰው» (45) ይላሉ።

እና ምርጫው «ተስፋ እና ተስፋ መቁረጥ ጎን ለጎን በሰፈኑበት፣ የንጋትና ብርሃን ጨለማን ተጎራርሰው በሚታዩበት…» (ዝ.ከ) የመጣ ምርጫ መሆኑን ይገልፃሉ። ይህ ወቅት፤ ታላቁ ደራሲ ቻርልስ ዲከንስ «የሁለት ከተሞች ወግ» የሚል ርዕስ በሰጠው መጽሐፉ እርሱ የነበረበትን ዘመን ሁኔታ በገለጸበት መልክ ሊታይ የሚችል ወቅት እንደሆነ አቶ በረከት ይጠቅሳሉ። ዲከንስ እንዲህ ይላል፤ «…ፍንትው ካለ ብርሃን ጎን ድቅድቅ ጨለማ ነበር። የተስፋ ጸደይ እንደ ሆነው ሁሉ፤ የጭንቀት ክረምትም ነበር። ሁሉም ነገር ከፊታችን ቢኖርም ማዕዳችን ባዶ የሆነበት ወቅት ነበር…» (45)።

እና ምርጫ 97፤ ኢህአዴግ ከናዳው ፍጥነት በላይ በመሮጥ ደማቅ ብርሃን መፍጠር ያልቻለበት ፤ ጨርሶም እንደ ዔሊ በማዝገም በናዳው ያልተጨፈለቀበት፤ ብርሃን እና ጨለማ ጎን ለጎን የቆሙበት ሁኔታ ውስጥ ገባ።

## «ከቀብር - መልስ»

ሆኖም ኢህአዴግ «ከቀብር መልስ» ሁኔታውን ከህብረተሰቡ ጋር በመወያየትና ጥናት በማድረግ እስኪረዳው ድረስ፤ ከምርጫው በፊት በታየው ዕድገትና በከተሞችም በተጀማመሩ ሥራዎች የተነሣ ህዝቡ እንደሚመርጠው ሙሉ እምነት ይዞ ወደ ምርጫው ገባ። ምርጫውን የገጽታ ግንባታ መሣሪያ ለማድረግም ስላሰበ (54)፤ እንዲሁም «በዶ/ር ነገደ ጎበዜ የተሰጠውን የምርጫ ግብና ስትራቴጂ ይዞ ወደ ምርጫ የገባው የእነ ዶ/ር በየነ ድርጅት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት በምርጫው ማሸነፍ እና ህገ-መንግስቱን ቀዳዶ መጣል፣ ይህ ካልተቻለም በአመጽ ሥልጣን ይዞ ህገ- መንግስታዊ ስርዓቱን መቀየር» (48) የሚል አቋም መያዛቸውንና ይህን የአመጽ እንቅስቃሴ ለማስወገድ ምርጫውን ፍጹም እንከን የለሽ በማድረግ ተቃዋሚውን ሰበብ ማሳጣት በሚል ሰፊ የውድድር ጎዳና መከፈቱን ያትታሉ።

«በከተማም በገጠርም መላ የአገሪቱ ህዝብ ከየትኛውም አጀንዳ በላይ በምርጫ ተግባር ተጠ ምዷል» የሚሉት አቶ በረከት (70) እርሶ አደሩ ከምርጫ ዘጠና ሰባት ሁለት ዓመታት ቀደም ሲል ጀምሮ፤ «ከአሮጌ ልማድ እየተጋፋን ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ከፍተኛ ርብርብ አደረግን። ለሁለት ተከታታይ ክረምቶች… አጫጭር ስልጠናና ትምህርት እንዲሰጠው

አደረግን፤... ማሳያ የሚሆኑ ሃብታም አርሶ አደሮች መፈጠር ጀመሩ...ተጻክሞ የኖረው የሥራ መንፈሱ መነቃቃት አሳየ... በዚህ ላይ ጊዜ የለንም በሚል ጥድፊያ... አርሶ አደርን በአግባቡ ሳያሳምኑ በልዩ ልዩ ተጽዕኖዎች በማንቀሳቀስ ሊፈፀሙ ይችላሉ ብለው ያመኑ አስፈጻሚ አካላት ሥራ ተጨምሮ ገበሬው አኩርፏል። በለውጡ መደሰት የጀመረ ቢሆንም ሥራ በዛብኝ ብሎ የሚያማርረው ደግሞ ቁጥሩ ጨምሯል። ከመቶ ሃምሳ የሥራ ቀናት አሳልፈን ሦስት መቶ ቀናት ለማሰራት ያደረግነው ጥረት ብልጽግናን ብቻ ሳይሆን የአካላዊ ድካም ጣጣ አምጥቷል... ልጆቹ እንዲማሩ... የፈረቃ ትምህርት ማስቀረታችን አጋዥ ጉልበት አሳጥቶ ድካሙን አብዝቶበታል» (ገጽ፣ 71) ይላሉ።

የከተማው ነዋሪም በተመሣሣይ ኩርፊያና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ነው። እናም የፖለቲከኞች ቅስቀሳ ታክሎበት፣ «የተቸገረ ህዝብ መሪዎቹን ይበላል» የሚል መልዕክት ቀርፀው የሚንቀሳቀሱት ተቃዋሚዎች ቅስቀሳ ተጨምሮበት ወጣቱ የሚታየው የብርሃን ጭላንጭል ሳይሆን ተቃዋሚዎቹ የሚነግሩት ጽልመት ሆነ። በዚህም ለከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ተጋለጠ።

«ኢህአዴግ የሁለት ዓመታት መልካም ሥራዎቹ ለራሱ ከፍተኛ እርካታ እንደ ፈጠረለት ሁሉ፣ ለህብረተሰቡም የሚታይ ተስፋ ፈንጥቋል ብሎ ያምን ነበር» (74) ሆኖም ውጤቱ ከዚህ ተቃራኒ ሆነ።

«የሽግግር ወቅት ህዝቡ ተስፋውን የሚያለመልምለት ነገር ሲያይ ድጋፉን... ተስፋው የደበዘዘ ሲመስለው ተቃውሞውን የሚግለፅበት ... ስክነት የማይታይበት ዘመን ነው» (88) የሚሉት አቶ በረከት፣ በምርጫ 97 የሚዲያ ክርክር ከመስከረም ጀምሮ እንደ ተካሄደና ተቃዋሚዎች ከሐምሌ 1996 ዓ.ም ጀምሮ ሦስተኛውን አገራዊ ምርጫ የአመጽ መንደርደሪያ ለማድረግ ቆርጠው መነሳታቸውን ይገልፃሉ። ይህም የተደረገው ተቃዋሚዎች መድረክ ጠበበን በሚል ሰበብ ለአመጽ ቀዳዳ እንዳያገኙ በር ለመዝጋት ጭምር ነበር። (63)

በምርጫ ክርክሩ ሂደት የነበረውን የድርጅቱን ቁመና ሲገመግሙ፣ «ኢህአዴግ በተፈጥሮው ሰርቶ በማሳየት የሚያምን፣ የሰራውን ጥሩ ሥራ ቅን ልቦና ያለው ሁሉ በቀላሉ ይመለከታዋል ብሎ የሚያምን... እንጂ የሰራውን ሥራ የሚያስተዋውቅ ድርጅት» (66) እንዳልሆነ፣ ስለዚህም ራሱን ለማስተዋወቅ ብዙም ትኩረት እንዳልሰጠ አትተዋል።

አክለውም፣ የምረጡኝ ዘመቻውና ክርክሮቹ በጠራ አኳኋን በተቀረፁ መልዕክቶች ላይ የተመሰረቱ እንዳልነበሩ፣ ስለዚህም ኢህአዴግ በሚዲያ ክርክሩ ያለ በቂ ዝግጅት እየገባ ይከራከር ስለ ነበር አንዳንዴ የረባ አቋምና ቁም ነገር በሌላቸው ተቃዋሚዎች በነገር አቀራረብ ተበልጦ እየተረታ መጓዙን አመልክተዋል።

ነገር ግን፣ የምርጫ ክርክሩ የምርጫውን ውጤት ውሰኗል የሚል እምነት እንደ ሌላቸው ገልፀዋል። አቶ በረከት፣ «በአገራችን የሚካሄዱ የምርጫ ክርክሮች ነገር ከሚሚቅ ባለፈ የምርጫ ውጤትን የሚወስኑበት ደረጃ ላይ የደረሱ አይደሉም። በመሆኑም የክርክሮቹ ፋይዳ የምርጫውን ውጤት እስከ መወሰን የደረሰ ነበር ሊባል አይችልም (67) ይላሉ።

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይገባል። የምርጫ ክርክሩ ፋይዳ ቢያንስ በርካታ መራጮች ለመምረጥ እንዲመዘገቡ በማድረግ ረገድ ያለው ሚና የሚያጠያይቅ አይሆንም። የምርጫ ቅስቀሳው የመራጮች ስሜት እንዲነሳሳ እና ለምርጫው ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ፣ በሂደቱም ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደረገ ይመስለኛል።

ምሁራን የምርጫ ሂደትን የሚወስኑ ብለው የሚጠቅሷቸው 12 ሂደቶች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ እጅግ ወሳኝ በሚል የሚለይዋቸው ሦስት ጉዳዮች ናቸው። አንደኛው የምርጫ ቦርድ (አስተዳደር) አደረጃጀት፣ ሁለተኛው የመራጮች የምዝገባ ሂደት፣ ሦስተኛው፣ የምርጫ ዘመቻ ናቸው።

ታዲያ አቶ በረከት የምርጫውን ውጤት ወስኗል ብለው የሚያስቡት ምንድነው? የሚል ጥያቄ ስናነሳ፣ ቁርጥ ያለ ምላሽ አናገኝም። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት፣ አቶ በረከት በትንታኔአቸው ውስጥ ለውጤቱ እና ለሂደቱ አስተዋፅዖ ያደረጉ በሚል የሚጠቅሷቸውን ነገሮች ለማውጣት እንሞክር። «ኢህአዴግ ህብረተሰቡን ከቆፈን ለማላቀቅ የሚያስችል ወይም ደምቆ የሚታይ የተስፋ ብርሃን መፍጠር አለመቻሉ፣ መራጩ ህዝብ መንታ ልብ በሚያስታቅፍ የሽግግር ዘመን ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፣ ተቃዋሚዎች ወጣቱ ያለውን የብርሃን ጭላንጭል እንዳያይና ተስፋ እንዲቆርጥ ለማድረግ እንቅልፍ አጥተው መስራታቸው፣ ኢህአዴግ በአግባቡ የተቀረፀና ዝግጅት የተደረገበት የቅስቀሳ መልዕክት ሳይዝ ወደ ክርክር መግባቱ ...» ወዘተ የሚሉ አስተያየቶችን እናገኛለን። እነዚህን ሀሳቦች ስናይ ደራሲው «የሚዲያ ክርክሩ የምርጫውን ውጤት ወስኗል» የሚል ሀሳብ እንዳላቸው እናስባለን። ሆኖም ተቃርኖው የሚፈታልን «ተቃዋሚዎች ያገኙት ድምፅ የተቃውሞ እንጂ የድጋፍ ድምፅ አለመሆኑን አልተረዱም» የሚል ሀሳባቸውን ስንመለከት ነው።

የተቃዋሚዎች ሀሳብ እና ፖሊሲ ህብረተሰቡን ለልማትና ለብልፅግና የሚያበቃ በመሆኑ የመረጣቸው ሳይሆን፣ በኢህአዴግ የአፈፃፀም ድክመት በመበሳጨቱ የወሰደው አቋም እንደሆነ እንረዳለን። ይህን ካየን ደራሲው ስለመራጮች ያላቸውን አስተያየት ደግሞ እንመልከት።

# መራጮች

ኢህአዴግ የምርጫውን ውጤት የመወሰን ሰፊ ድርሻ ያለው አርሶ አደሩ ነው ብሎ ያምናል። ትክክል ነው። እናም የምርጫው ወቅት በፍጥነት እየተቃረበ ሲመጣ «...አርሶ አደሩ ውሉን የማይስት መሆን አለመሆኑ የሚታይበት የምርጫ ዕለት እየተቃረበ ነበር። ...ቀደምት አርሶ አደሮች... የውጭ ጠላቶችን በመመከት በፅናት እንደቆሙት ሁሉ የዘመኑ አርሶ አደርም በዚህ የተጋጋመ የምርጫ ወቅት ይህችን አገር መታደጉን ይቀጥል ይሆን?» (72)

ደራሲው፤ ይህ ወሳኝ ሚና ያለው አርሶ አደር ከዘጠና ሰባት ምርጫ በፊት ያለበትን ሁኔታ ሲገመግሙ «... አርሶ አደሩ በአንድ በኩል በልማት ሃሳባችን የሚደሰት፣ በሌላ በኩል ከአፈፃጸም አኳያ በታዩ ድክመቶች ደግሞ የተማረረ አርሶ አደር ሆኗል።...በመለወጥና ያለፈውን በማቆየት ፍላጎቶች መዋለል የጀመረው የአገራችን አርሶ አደር በማንኛውም የሽግግር ህብረተሰብ ውስጥ እንደሚገኝ አርሶ አደር የሽግግር ባህሪያትን መላበስ ጀመሯል። ሥራ አበዛችሁብኝ ብሎ እያማረረ ለገበሬ የሚያስብ መንግስት ያገኘሁት አሁን ነው ብሎ ይመርቃል። ፋታ ነሳችሁኝ ባለበት አንደበቱ ለእኔ ብላችሁ እኮ ነው የምትደክሙት ይለናል። ያለፈውን የዕረፍት ዘመን ከልቡ እየናፈቀ በድካሙ ፍሬ ጎተራው በመሙላቱ ይደሰታል። ማረፍ እየፈለገ ነገ ስለሚሰራው ያስባል። በትጋት፤ በደስታና በመመረር፣ በሳቅና በለቅሶ መካከል የሚዋልል እውነተኛ የሽግግር ወቅት ገበሬ» (72)

የወጣቱም፣ የነጋዴውም በአጠቃላይ የህብረተሰቡ ሁኔታ በዚሁ የሽግግር ወቅት ባህርይ ተተንትኖ ቀርቧል። የምርጫ ታዛቢውም የቀለም አብዮት ዓላማ ይዞ ወደ ሂደቱ የተቀላቀለ መሆኑን ያወሳሉ። አቶ በረከት ስለ ምርጫ ታዛቢው ሲገልፁ፤ «...የቀለም አብዮት እስከ ማቀጣጠል የሚሄድ አንድ ኢንዱስትሪ መሆኑ እያደር ግልፅ ሆነልን» ይላሉ። አያይዘውም፤ «አይ. አር. አይ. የተባለና ከኒዮሊበራል ርዕዮት አራማጆች አንዱ የሆነው ይኸው ተቋም በምርጫው እንዲሳተፍ ሳይጋበዝ በሰፊው በተከፈተው በር ያለ ጠያቂ ገብቶ በይፋ ለተቃዋሚዎች ያደላ ሥራ ሲሰራ እጅ ከፍንጅ ተያዘ» (78) ይላሉ። በዚህም የአሜሪካ መንግስት መቆጣቱን እና ሁለት መግለጫዎች ማውጣቱን፤ ሆኖም መንግስት መግለጫውን ንቆ ማለፉን ይተርካሉ።

ስለነጋዴው የህብረተሰብ ክፍል ሲገልፁም «ለወትሮው አትራፊ ለሆኑ የንግድ ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት...የፖለቲካ ጉዳይን ራቅ ብሎ የሚያይ» (85) ሲሉ የገለፁት ባለ ሀበት እንኳን ወደ ምርጫው ራሱን እንዳስገባ፣ «...እንደዋዛ ያገኘውን ብር ሲመዘው አምሽቶ ሲበትነው እንደሚያድር» እና «ፓርቲዎች በሚጠሩት ስብሰባ ላይ ሁሉ መገኘት እንደ ጀመረና

በተገኘበት መድረክ ግንባሩን ከማስመታት አልፎ ለሁሉም የማሸነፊያ ምክሩን እንደሚሰጥ፣ ለተቃዋሚ የነገረውን የማሸነፊያ ስትራቴጂ ሳይጨምር ሳይቀንስ ለኢህአዴግም እንደሚለግስ፣ ለኢህአዴግ የነገረውን ስልት ለተቃዋሚዎች እንደሚመክር ለሁለቱም ብር» እንደሚበትን ይገልፃሉ። (86/87)

ህብረተሰቡ በሚያዚያ መጨረሻ ኢህአዴግና ተቃዋሚዎች ኃይላቸውን ለመፈተሽ በሁለት ተከታታይ ቀናት የድጋፍ ሰልፎችን ጠሩ። የድጋፉ ሰልፉን ቅዳሜ ሚያዚያ 29/1997 ዓ.ም የጠራው ኢህአዴግ ነበር። «ኢህአዴግን እደግፈዋለሁ፣ እመርጠዋለሁ» የሚል አቋሙን ለመግለፅ የወጣው የአዲስ አበባ ህዝብ፣ መስቀል አደባባይን ሞልቶ ታየ። የሰልፉ ትልቅነት ኢህአዴግ በአዲስ አበባ አሸንፋለሁ የሚል ስሜት እንዲይዝ ያደረገና በተቃዋሚዎች ሰፈር ሽብርን የነዛ ሆኖ አለፈ። ስለዚሁ ሰልፍ አቶ በረከት ሲገልፁ፣ «በሰልፉ የልብ ልብ የተሰማው ...አቶ መለስም በዚህ ሰልፍ ላይ የተሳተፉትን ሰዎች ድምፅ ማንም ሊጠራጠር እንደማይችልና እንደማይገባ እስከ መግለጽ ደረሰ» (87) ይላሉ።

በማግስቱ ሚያዚያ ሰላሳ «ሁለት መቶ ሺህ ሰው ይወጣልናል የሚል ግምት ያልነበራቸው» (87) ተቃዋሚዎች የድጋፍ ሰልፍ ጠሩ። ደራሲው ስለዚህ ዕለት ክስተት ሲገልፁ፣ «...ሰልፍ መጠ ራቱን ስለመስማቱ የምትጠራጠረው ሁሉ ከየቤቱ እየወጣ ወደ መስቀል አደባባይ ተመመ። ...መስቀል አዳባባይ ጢም ብሎ ከመሙላት አልፎ ወደ ዳር እና ዳር ፈሰሰ። ኢህአዴግ በጠ ራው ሰልፍ ላይ የተካፈለው አብዛኛው ሰው ባልተገኘበት ያን ያህል ህዝብ በአደባባይ ሊገኝ አይችልም። በመሆኑም፣ አንዳንዶቻችን ቅዳሜ ዕለት ኢህአዴግን ደግፈው የተሰለፉትም ቢሆን በዚህኛው ሰልፍ ላይ መውጣታቸውን አምነናል» (88) ይሉና የዚህን አስገራሚ ክስተት ፍች «ደግሞስ የሽግግር ወቅት አይደል?» (ዝ.ከ) በማለት ይደመድማሉ።

ከዚሁ ድጋፍ ሰልፍ ጋር ተያይዞ አንድ አስገራሚ የሆነባቸው ነገር እንዳለ ይጠቅሳሉ፣ «...አንድም ሰው የቀረ ከማይመስልበት የተቃዋሚዎች ሰልፍ መካከል ግን አንድ ሰው ብቻ አልተገኘም» ይሉና ይህ ሰው «...በተራ ጉዳዮች ሳይቀር የአራድነት ብልጫ የሚሰማው ስለሚያዚያው ሰልፍ ተናግሮ የማይሰለቸው...» (91) በሚል የሚገለፅዋቸው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ መሆናቸውን በመገረም ነግረውናል።

እናም በዚህ ርዕስ ያነሱትን ትረካ ሲያጠቃልሉ «ኢህአዴግ በተቃዋሚዎች የድጋፍ ሰልፍ ግብታዊነት ላይ ጥርጣሬ ባይኖረውም የሰልፉ ትልቅነት እልህ አጋብቶታል» (91) ካሉ በኋላ እንደገና ኃይሉን ለመገንባትና የሚዋልል ልብ ያላቸውን መራጮች ለማፅናት ምሽት ላይ በየወረዳው የሻማ ማብራት ስነስርዓት ለማካሄድ መወሰኑን ይጠቅሱና፣ «ነገር ግን የአዲስ አበባን

ነዋሪ የምርጫ ውሳኔ የሚያስቀይር ውጤት አልነበረውም። ...የከተማው ህዝብ ኢህአዴግን ላለመምረጥ ወስኗል» ይላሉ።

አያይዘው፣ «ወደ ድምፅ መስጠቱ ሂደት ስናመራ የአዲስ አበባን ውጤት በተሳሳተ ደረጃ የገመተው ኢህአዴግ ብቻ ነበር። ... ቆጠራው እስኪካሄድ ድረስ ተቃዋሚዎችን በዝረራ እናሸንፋለን እያልን የራሳችንን ግምት እያነበብን ተጓዝን። በብዙ ከተሞች ግድግዳ ላይ በትልቁ የተፃፈውንና ለገማች ብቻ ሳይሆን፣ የህዝብ አስተያየትን አስቀድሞ ለማወቅ በሚያስችል ጥናት ሊታወቅ ይችል የነበረውን የህዝብ ስሜት ማንበብ እንዳቃተን እሁድ ደረሰ» (92) በማለት የምረጡኝ ዘመቻ ሂደቱን ትረካ ይደመድማሉ።

# ውጤቱ

ቀጣዩ ምዕራፍ (ሦስት) የድምፅ  መስጠት ሂደቱንና ቆጠራውን የዳሰሱበት ምዕራፍ ሲሆን ስሜትን ሰቅዘው የሚይዙ ክስተቶች የተገለጹበት፣ ትረካው እንደ ግሩም ተውኔት ሴራው ከፍተኛ ጡዘት ላይ የሚደርስበት ምዕራፍ ነው። የሴራው ልቀት (Denouement) ምን መልክ እንደ ያዘም የምናይበት ምዕራፍ ነው።

የምርጫ ታዛቢዎች ሳይቀሩ «ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ሰላማዊ የምርጫ ሂደት ብለው ለማድነቅ በተገደዱበት» (96) ሁኔታ የተከናወነው ሂደት ወደ ድምፅ መስጠት ተሻግሮ ሁሉም ተፎካካሪዎች ቁጭ ብለው አድረው የሚጠብቁት የድምጽ ቆጠራ ውጤት መውጣት ጀመረ። በዚያ ጊዜ የኢህአዴግ ምርጫ ኮሚቴ ውስጥ ሲሰሩ ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱ የሆኑት አቶ በረከት «የወራት ድካም ስለተጫጫናቸው» ምሽቱን አረፍ ብለው ጧት ማልደው ለመምጣት ወደ ቤታቸው ሄዱ።

እርሳቸውና ሌሎች የተወሰኑ ጓዶች ወደ ቤት ሲሄዱ ቀሪዎቹ የቆጠራውን ውጤት ሲከታተሉ አመሹ። ከዚህ በኋላ ስለሆነው ሲገልፁ፣ «እኔም ውጤቱ መልካም እንደሆነ አስቤ ጋደም ብልም ወደ አምስት ሰዓት ገደማ ባለቤቴ ከእንቅልፌ ቀስቅሳ፣ ‘እረ የምርጫው ውጤት ጥሩ አይደለም። ከየክፍለ ከተማው የሚመጣው የቆጠራ ውጤት ኢህአዴግ እንደሚሸነፍ የሚያመለክት ነው’ አለችኝ» ይላሉ። የሽንፈት ዜናውን እንደሰሙ «... ግራ በተጋባ ስሜት የነገረችኝን ስሰማ ብዙም ሳልቆይ ወደ ኢህአዴግ ቢሮ አመራሁ» (97) ይሉናል።

እዚህ ላይ አንድ የገረመኝ ግጥምጥሞሽ አለ። ይህ የምርጫ ዘጠና ሰባት ውጤት የሚገለፀው በመጽሐፉ ገጽ 97 ነው። የሆነ ሆኖ አቶ በረከት፣ ቢሮ ሄዱ። እርሳቸው ቢሮ እስከደረሱበት የተጠናቀረውን የምርጫ ውጤት ተቀብለው ከተመለከቱ በኋላ፣ «...በአዲስ አበባ ምርጫ እንደ ተሸነፍን ተገነዘብኩ» (97) ይላሉ። አክለውም፣ «ጥቂት ቆይቶ አቶ መለስ ከቤቱ ደውሎ ስላለው ሁኔታ መረጃ እንድሰጠው ጠየቀኝ። ሁሌም ስንገናኝ እንደሚለው «ሰውዬው» የሚለውን አገላለፅ አስቀድሞ የከተማው ውጤት አላማረም መሰል በማለት ቢጠይቀኝም፣ ከእኔ በፊት ጀምሮ ሁኔታውን ይከታተል ስለ ነበር የውጤቱ አለማማር ለእኔ እንጂ ለእርሱ እንግዳ አልነበረም። የእኔም ትዝብት እንደዛው መሆኑን ገልጬለት...ሁኔታው ለውጥ እንደማይኖረው ካረጋገጥኩ በኋላ ብዙም ሳልቆይ ወደ ቤቴ ተመለስኩ» (97) ይላሉ።

ይቆጠራው ሂደት ተጠናቀቀ። ከዚህ በኋላ የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተሰበሰበ። አቶ መለስ የወቅቱን ሁኔታ የሚገልፅ እና መፍትሄም የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጁ። ሪፖርቱም «ተዓማኒ ምርጫ እንደተካሄደና የማሸነፍ ግቡ እንደ ተሳካ፣ ...የተገኘው ውጤት ከሦስት ዓመታት በፊት ሊያጋጥም ይችላል ስንለው ከነበረው አርማጌዶን ጋር የሚመሳሰል ባህርይ እንዳለው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተሀድሶ እንቅስቃሴው ገና የሚፈለገው ደረጃ ላይ ባይደርስም የነፍስ አድን መሳሪያ መሆኑ የተረጋገጠበት ምርጫ እንደሆነ መግባባት ላይ ተደረሰ» (125/26) ብለዋል።

ከዚህ በኋላ የኢህአዴግ ጥረት ህዝቡን የሚያስቀይም ስህተት አለመስራት እና አመጽ እንዳይቀሰቀስ ጥረት ማድረግ መሆኑን ደራሲው በተደጋጋሚ እየገለፁ ትረካው ይጓዛል። በዚህ ዓይነት ስሜትን የሚነኩ ትዕይንቶች እየተረኩልን ወደ ድህረ ምርጫው ሂደት ይሸጋገራሉ። በመጨረሻም ሰላማዊው ሂደት ወደ ቀውስ ያመራል። በዚህ የትረካው ክፍል (ምዕራፍ አራት) አመፁን ለማስቀረት ወይም እንዳይስፋፋ ለማድረግ ድርጅቱ ያደረገውን ወገብ የሚሰብር ጥረት፣ የጎዳና ላይ አመጽ፣ ክስተቶችን የአውሮፓ የምርጫ ታዛቢ ቡድን በሂደቱ የነበረውን ሚና፣ በተለይም የወ/ሮ አና ጎሜዝን እና የአንዳንድ የምዕራብ ሀገራት ዲፕሎማቶችን ፈር የሳተ አፍራሽ ሚና፣ በአመፁ ቅስቀሳ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ተግባር ወዘተ በሰፊው የሚነበብበት መሳጭ ትረካ ይቀጥላል። ከወ/ሮ አና ጎሜዝ እና የአውሮፓ ኮሚሽን አምባሳደር ቲም ክላርክ ጋር ተያይዘው የሚነሱት ትረካዎች የሂደቱን እየከረረ መሄድ ከማመልከት ባሻገር «ድራማቲክ» መልክ ያላቸውም ናቸው። የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን የምዕራብ ሀገራት አምባሳደሮች ሁኔታ አላምር ያላቸው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በእንግሊዝኛ የፃፉትን ፅሁፍ ተከትሎ የፈጠረው መደናገጥ ተውኔታዊ እዩኝታ (appeal) ያለው ነው።

ስለ አውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን አቶ በረከት ሲገልፁ፤ «የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች ቡድን መሪ ወ/ሮ አና ጎሜዝ አሸንፋችኋል የሚል ሪፖርት ለተቃዋሚዎች በሰጧቸው ሰሞን አምባሳደር ቲም ክላርክን አግኝቼ ይህ ትክክል እንዳልሆነ ስገልፅላቸው፣ የታዛቢ ቡድኑ በቀጥታ ከእርሳቸው ቁጥጥር ውጪ እንደሆነና ጉዳዩ የማይመለከታቸው መሆኑን በመግለፅ መልሰውልኝ ነበር» (137) የሚሉት አቶ በረከት፤ ሆኖም ሰውዬው በጉዳዩ ውስጥ እጃቸውን ያለልክ የሚያስገቡ መሆናቸውን ይገልፃሉ::

«በሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ አና ጎሜዝ ሚዛኑን ጠብቄ አዘጋጅቻለሁ ያሉትንና የአፋጀነት ሚና የተጫወቱበትን ሪፖርት በተኑ:: ሪፖርቱ ከዚህም አልፎ ስለቀጣዩ የመንግስት ምስረታ ጉዳይ መመሪያ ቢጤ መስጠትም ይቃጣዋል:: ...ሁላችንም ሪፖርቱ ደርሶን ከተመለከትነው በኋላ በአውሮፓ ህብረት አድራጎት ከባድ ቅሬታ ተሰምቶናል:: አቶ መለስ... ለሪፖርቱ የሚሆነውን ምላሽ... ማዘጋጀቱንና እየላከለኝ እንደሆነ ገለፁልኝ» (146/7) ካሉ በኋላ፤ «...የአቶ መለስ ፅሁፍ በቁም ነገር የተሞላና ለዛ ያለው ብቻ ሳይሆን በሴትየዋ ስነ- ምግባር ዙሪያ ሽሙጥ በመቀላቀል የቀረበ ነበር:: ሴትየዋ በአንድ የፕሬስ መግለጫ ላይ በግልፅ እንዳመኑት ዶ/ር ብርሀኑ በሸራተን ሆቴል በያዙት ክፍል እንዲደበቅ አድርጌዋለሁ ብለው ነበር... አቶ መለስ ለወይዘሮዋ ሪፖርት በሰጠው መልስ ይሄን መነሻ በማድረግ የተዋቂዋን አቀንቃኝ የቲና ተርነርን ግጥም ተውሶ ‘what’s love got to do with it’ (ፍቅርን እዚህ ውስጥ ምን ዶለው?) ብሎ አሽሙር ቢጤ ጣል ያደረገበት ቦታ ስደርስ ብቻዬንም ብሆን ከጣራ በላይ ሳቅሁ:: ከስንት ቀናት ውጥረት በኋላ ከልቤ የሳኩበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም» (148) ሲሉ የወቅቱን ሁኔታ ያወሳሉ::

ይህ ፅሁፍ ከወጣ በኋላ ስለተፈጠረው ሁኔታ ሲተርኩ፤ «የአቶ መለስ ፅሁፉ በሦስት ክፍል ተቆራርጦ በአዲስ ዘመን እና በሄራልድ ላይ ቀረበ:: የመጀመሪያው ክፍል በታተመ ማግስት ግን አንድ ያልተለመደና የሚገርም ክስተት አጋጠመኝ:: ፀሀፊዬ በወቅቱ የአሜሪካን አንባሳደር የነበሩት ኦሬሊያ ብራዚል በድንገት ወደ ቢሮዬ መጥተው ሊያነጋግሩኝ እንደሚፈልጉ ገልፀው እንግዳ መቀበያ አካባቢ እንዳሉ ነገረችኝ:: ቀጠሮም ባይኖራቸው ላነጋግራቸው እንደምችል ጋበዝኳቸው:: ከአምባሳደሯ ጋር ግን ያልጋበዝኳቸው የአውሮፓ ህብረት አምባሳደር ቲም ክላርክ፣ የእንግሊዝ አምባሳደር ቦብ ዲዋርና የኦስትሪያ አምባሳደር ወ/ሮ ብሪጅት አብረው ስለነበሩ ሳያስፈቅዱኝ ተከታትለው ወደ ቢሮዬ ገቡ:: ... የአሜሪካን አምባሳደር አንዳችም ቅሬታ የሌላቸው ቢሆንም ሦስቱ አምባሳደሮች ጎትተው እንዳስገቧቸውና የአሜሪካን ታላቅነት መጠጊያ እንዳደረጉት ለመረዳት አላዳገተኝም:: ...የእንግሊዝ አምባሳደር ሚስተር ቦብ ዲዋር ወደኔ የመጡት «ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአውሮፓ ህብረት መስጠት በጀመሩት ምላሽ ተከፍተው እንደሆነና ...ነገርዬውን ...እንድናረግበው ይህን ካላደረግን ከፍ ያለ ዋጋ እንደምንከፍል ለማስረዳት እንደሆነ እየተቅለሰለሱ ገለፁልኝ:: አምባሳደር ቲም ክላርክ በፋንታቸው ደግሞ

«አቶ መለስ ረጅም ርቀት ሄደዋል ይሄ ፅሑፍ መቆም አለበት» በማለት አጉል ድፍረትና ጅላጅልነት የተቀላቀለበት መመሪያ ቢጤ ሊሰጡኝ ሞከሩ» ይላሉ።

አክለውም፤ «...እነዚህ ጉዳኞች ከማን መንግስት ጋር እንደሚነጋገሩ እንዳልገባቸው፣ ስለዚህም ልክ ልካቸውን ልነግራቸው ወሰንኩ... የአቶ መለስም ፅሑፍ በተያዘለት ዕቅድ መሰረት ይታተማል አ.ይ.ቋ..ረ..ጥ..ም!!» (151/52/53)፡ የሚል መልስ እንደሰጧቸው ይተርካሉ።

«...ይዘውት ለመጡት ያልተገባ ሀሳብ በልህና በምሬት መናገሬ አስደንግጧቸዋል። ሆኖም የመጨረሻ ማስፈራሪያቸውን ሳይተኩሱ መሄድ አልፈለጉም። የእንግሊዙ አምባሳደር የፅሁፉ መታተም ካልተቋረጠ እርዳታ ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል ብለው በግላጭ ነገሩኝ። እርዳታችሁን ይዛችሁ ወደ ፈለጋችሁት ሂዱ አልኳቸውና በዚህ ተለያየን። ከቢሮዬ ሲወጡ የአሜሪካን አምባሳደር ለአንድ ደቂቃ ዕድል ስጠኝ ብለው ወደ ኋላ ቀሩ። ሁሉም መወጣታቸውን እንዳረጋገጡ 'አሁን የተናገርከው አሜሪካንን ይመለከታልን?' በማለት ግለፅ ጥያቄ አቀረቡልኝ። አይ እናንተን አይመለከትም የሚል ነበር መልሴ... እርሳቸውም ከአቶ በረከት ቢሮ እንገናኝ ብለው ስለላኩባቸው እንደመጡ፣ እዚህ እንደተገናኙ ደግሞ ለምን እንደ ተጠሩ መጠ የቃቸውንና 'የኢትዮጵያ መንግስት ያደፈ ጨርቁን በአደባባይ ሲያጥብ እንድትታዘቢ ነው' የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው አወሱልኝ። ልትሰራ ሄዳ ተላጭታ መጣች አለ ያገሬ ሰው» (53) በማለት ትረካቸውን ያጠቃልላሉ።

በአጠቃላይ የ2002 ምርጫ፤ የኢህአዴግ አመራር ከራሱ ስህተቶችና ከሌሎች ... ልምድ ተምሮ ኢትዮጵያን... ከአፍሪካ ነብሮች አንዷ ሊያረጋት መቃረቡን የሚጠቅሱት አቶ በረከት፤ «ይህም ድርጅቱ ከስህተቱ የመማር በጎ ልምዱ ውጤት ነው» ይላሉ። በዚህ ክፍል ትረካ የድርጅቱ ነባር አመራር ቦታውን ለአዲሶቹ የማስረከብ ሂደት መጀመሩን እናነባለን። ለኢትዮጵያ አዲስ የሆነው ይህ የመተካካት ሂደት «ሲሰራ እንጂ ታሪክ ሲያወራ ያልኖረው አመራር... ከእንግዲህ የቀረው ያልተነገረ ታሪኩን መንገር ሊሆን ይችላል» ካሉ በኋላ፤ «...የተሰሩና ያልተነገሩ ታሪኮች ለህዝብ እንዲቀርቡ፤ ሌላውም ለካ እንዲህ ነበር እያለ የድርሻውን ለማንሳት ይተጋ ዘንድ፤ ከፊት መስመር ገለል ያሉት ሁሉ አንደበታቸው ሊያፍታታ፤ ብዕራቸው ሊከትብ የሚገባው ወቅት ላይ ደረስን። ይህም ጽሁፍ ከለመድነው ሥራ ወደ ታሪክ ነጋሪነት በመሸጋገር ሂደት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ» (313) በማለት ወጉን ይፈፅማሉ።

ዲከንስ «የሁለት ከተሞች ወግ» ሲል የሰየመው ልብ ወለድ መቋጫ ሆኖ የምናነበው ቃል፤ በ«የሁለት ምርጫዎች ወግ» ዳግም የታሪክ መቋጫ ሆኖ መጥቷል። ይህ የመጨረሻ ቃል፤

«ከእንግዲህም ከዚህ ቀደም ከሰራሁት እጅግ- በጣም እጅግ በጣም- እጅግ ወደ ተሻለ እፎይታ አመራለሁ» እያለ የሚሄድ ሲሆን፤ አቶ በረከት በማያያዝ፤ «በዚህ አጋጣሚ ለእኛው ዘመን የታጋይ ትውልድ የተሻለ የሥራና የእፎይታ ዘመን በመመኘት ብሰናበትስ» በማለት ትረካቸውን ይዘጋሉ (314)::

በጥቅሉ «የሁለት ምርጫዎች ወግ» ድንቅ መጽሀፍ ነው:: አቶ በረከት እንዲህ፣ የሀሳብ ጥራት፣ የተገራ ስሜት፣ ንድፈ- ሀሳባዊ ዕይታ፣ የአፃፃፍ ለዛ ያላቸው ደራሲ ናቸው::